# ዓባይ፣ ግብፅ፣ ሻዕቢያ እና "ሶስተኛው ምላሱ"

**ማህደር አለባቸው 04/28/13**

**(ክፍል አንድ)**

"ያሰብከው ነገር አልሳካ ብሎህ ዓላማህ ሲጠጥር፣ ጠማሩን ተውና የላላውን ወጥር" ይል ነበር አንድ ወዳጄ–ቀደም ሲል አስቦት የነበረው ነገር አልሳካ ሲለውና ጉዳዩን በሌላ መልክ ለመጀመር ሲፈልግ፡፡ የዚህን ወዳጄን አባባል ያነሳሁት ያለ ምክንያት እንዳይመስላችሁ– ነገሩ የኤርትራው አምባገነን መሪ የአባይ ወንዝ አጠቃቀምን አስመልክተው በየጊዜው ከሚሰጡት የተምታታ አቋም ካለው መግለጫቸው ጋር መመሳሰሉ አስደምሞኝ እንጂ…

… መቼም ውድ አንባቢዎቼ "እንዴት?" ማለታችሁ አይቀርም፡፡… ጉዳዩ ግን እንዲህ የሚነበብ ነው፡፡… በአቶ  ኢሳያስ የሚመራው የትርምስ ቡድን፣ በትናንት አቋሙ ዛሬ አይፀናም፣ የዛሬውንም ነገ ላይ አይደግመውም፡፡ በተለይም የቡድኑ ቁንጮ በየጊዜው በሚያስደምጡን "ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ" አይነት ዲስኩር "በአንድ ራስ ሁለት ምላስ" የሚለውን ሀገርኛ ብሂል ተሻግረዋል ማለት ይቻላል–በአንድ ራስ ሶስት ምላስ ሆነው። እናም "በአንድ ራስ አሥር ምላሽ" ያላቸው ይመስል፣ በየጊዜው የሚያሰሙን ማደናገሪያዎች የማንነታቸው መገለጫ ሆነው ከቀጠሉ፣ እነሆ ሁለት አሥርት ዓመታትን ተሻገሩ፡፡…

ታዲያላችሁ "ወዲ አፎም" ሀገራቸው ለአባይ ወንዝ የምታበረክተው ጠብታ ውሃ ሳይኖር፣ በወንዙ ከባቢ የሚገኙ በመሆናቸው ብቻ የተፋሰሱ ሀገራት "ታዛቢ" እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህን የታዛቢነት ሚናቸውን ተመርኩዘው በየወቅቱ የሚናገሩት እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ አስተያየቶች ለሰሚው ግራ እያጋቡ ዛሬ ላይ ደርሰዋል፡፡…

…የአልጀዚራ ቴሌቪዥን ከፍተኛ የፖለቲካ ተንታኝና "ኢምፖየር" (Empire) የተሰኘውን ኘሮግራም የሚያሰናዳው ማርዋን ባሻራን የተባለው ጋዜጠኛ እንዲህ አይነት ነገር ሲያጋጥመው "አቋም ያልሆነ አቋም" ማለት ይቀናዋል፡፡ ያኔ በሊቢያ የተፈጠረውን ቀውስ ተከትሎ የኮሎኔል ጋዳፊ ባለሥልጣናት ይሰጡት የነበረውን የተምታታ አስተያየት እያደመጠም "እነዚህ ሰዎች አቋም አልባ አቋም ነው የሚያራምዱት" በማለት እየደጋገመ ሲተቻቸው ሰምቻለሁ፡፡… እኔም ለዛሬው የእርሱን ቃላት ተዋስኩኝ፡፡ እናም አፈሩን ያቅልላቸውና የልብ ወዳጃቸው ከነበሩት ጋዳፊና ባለስልጣኖቻቸው እንዲህ ዓይነቱን "አቋም የለሽ" መርህን የወረሱት የአቶ ኢሳያስን ሽፍጥ ለማሳየት ወደድኩ–ልክ እንደ ትሪፖሊዎቹ የቀድሞ ባለሥልጣናት በአባይ ወንዝ ላይ የሚያራምዱትን መርህ

አልባ አቋም፡፡  ምንም እንኳን ነገሩ "ከአህያ ጋር የዋለች ጊደር ምንትስ ተምራ ትመጣለች" እንደሚባለው ቢሆንም፣ የሰውዬውን አቋም የለሽ "አቋም"ን በጥቂት ዓመታት ልኬት ውስጥ ብቻ የኋሊት በመጓዝ እንዲህ ላስቃኛችሁ ፈቀድኩ፡፡…

…ጊዜው ብዙም ሩቅ አይደለም። በ"አንደኛው ምላስ" ከተነገረ። እ.ኤ.አ. በ14/05/2010 ዓ.ም ነው። ኢትዮጵያን ጨምሮ አራት የላይኛው የአባይ ተፋሰስ ሀገሮች /ከግብጽና ከሱዳን ውጪ/ በወንዙ አጠቃቀም ላይ የነበሩትን የቅኝ ግዛት ውሎች የሚተካ አዲስ የስምምነት ማዕቀፍ ተፈራረሙ፡፡…ኢሳያስ አፈወርቂ ግን በዚያች ምሽት ተኝተው ያደሩ አይመስልም፡፡…እንዲያውም "አባይን ተሻግሮ አባይ አለ ወይ፣ ሞትና ፀረ-ልማትነት አንድ አይደለም ወይ?" እያሉ ለራሳቸው ሲያንጐራጉሩ ያመሹ ይመስላል፡፡… አይነጋም የለምና ጨለማው በብርሃን ተተካ። ተግባርና ኃላፊነቱንም ለብርሃን አስረከበ፡፡…"ወዲ አፎም"ም ያደረ አፋቸውን ሳይሸሩና ፊታቸውን ሳይታጠቡ በማግሥቱ በግብጽ የቴለቪዥንን መስኮት ብቅ አሉ፡፡… "ምን ሊነግሩን ነው?" በማለት ልቤ ከፉኛ ተሰቀለ፡፡…

… ሰውዬው የምናውቃትን መጫሚያቸውን ተጫምተውና እግራቸውን አነባብረው፣ ለግብፁ ጋዜጠኛ እንዲህ አሉት… "የላይኛው ተፋሰስ ሀገሮች በአባይ ውሃ አጠቃቀም ላይ የፈፀሙት የተሳሳተ ስምምነትና የመተዳደሪያ ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይህ ውሣኔያቸው በመካከላቸው ያለውን ችግር ከማባባሱም በላይ ውጥረት ውስጥ ይከታቸዋል፡፡"… እናንተዬ ነገሩ እንዴት ነው?!– ጐሽ የኔ የሙባረክ ነጭ ለባሽ አትሉም እንዴ?- አዎ! አቶ ኢሳያስ የሙባረክን መንግሥት ያረጀ፣ ያፈጀ አስተሳሰብ ጉዳይ ፈፃሚ ለመሆን ሌሊት እንቅልፍ  በዓይናቸው ሳይዞር  አድሮ፣ ጧት "የቁርጥ ቀን ልጅነታቸውን" አሳዩን፡፡… እኛም "ብራቮ የክፍለ ዘመናችን ምርጡ የውጥረትና የጦርነት ተንታኝ ብሎም አቀንቃኝ" ስንል በወቅቱ ተሳለቅንባቸው፡፡…

… ኢሳያስ አፈወርቂ ግን "ወይ ፍንክች የአባ ቢላዋ ልጅ" ብለው፣ በየጊዜው በአባይ ወንዝ ጉዳይ የቀድሞው የግብጽ መንግሥት አጋር መሆናቸውን ሲነግሩን ከረሙ፡፡ እኛም ማንነታቸውን ጠንቅቀን ስለምናውቅ "ወዲ አፎም- ለምን?" ብለን አልጠየቅናቸውም፡፡ ምክንያቱም ከእርሳቸው ሊገኝ የሚችል ምላሽ ሊኖር ስለማይችልም ነው። እናም እውነታውን ራሳችን እንዲህ ገላልጠን እንመለከተዋለን፡፡..

ውድ አንባቢዎቼ እንደምታውቁት፣ በምሥራቅ አፍሪካ መረጋጋትና ሰላም እንዳይኖር "ሱባዔ" በመግባት ጭምር የሚፀልዩት እኚህ የአሸባሪዎች መሪ፣ በተፋሰሱ ሀገራት ውስጥ "ውጥረት ይፈጥራል" ያሉት በአባይ ወንዝ ምክንያት የቀቢፀ-ተስፋ ጦርነት ናፋቂ ህልማቸው ከሁለት ምክንያቶች የመነጨ ነው፡፡ አንደኛው የቀድሞውን የግብጽ መንግሥት በመደገፍ ለፀረ-ሰላም

ኃይሎች የጥፋት ተልእኮ የሚውል ገንዘብ ማግኘት ሲሆን፣ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ "ሁሉም ሀገራት ይሳሳታሉ፣ የእኔ አመራር ግን ትክክል ነው" ከሚል አላዋቂ ግብዝነት የተሰነዘረ ሃሳብ ነው፡፡

ሰውዬው በአባይ ወንዝ ሳቢያ በተለይም ግብጽና ኢትዮጵያ ውጥረት ውስጥ ቢገቡ ተጠቃሚ እሆናለሁ ብለው የሚያስቡ የነውጥ ተስፈኛ ናቸው፡፡ ማንም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው፣ የቀድሞው የግብጽ መንግሥት ኢትዮጵያ ሰላም ከሆነችና ከተረጋጋች አባይን ልትገድብ ትችላለች በሚል ተቀባይነት በሌለው ኢ-ፍትሐዊ እሳቤ የኤርትራን መንግሥት በነጭ ለባሽነት ሲያሰማራው ነበር፡፡ አቶ ኢሳያስም በ"ጭር ሲል አልወድም" ባህሪያቸው እንደ ውሃ ቀጂ በየቀኑ ካይሮ እየተመላለሱ፣ ሀገራችንን እንዴት ማተራመስ እንደሚቻል ለሙባረክ ማብራሪያ በመስጠት ባተሌ ሆነው ቆይተዋል–የዛሬን አያድርገውና። ለዚህ ተግባራቸውም በወረታው ዶላሮችን የሚቃርሙት የአሸባሪዎቹ መሪ፣ ሀገራቱ በአባይ ወንዝ ዙሪያ ስምምነት ላይ ከደረሱና ሰላም ከወረደ "የእንጀራ ገመዴ ይበጠሳል" በማለት የሚሰጉና "የዕለት እንጀራዬን ብጥብጥ አድርገው" እያሉ የሚያላዝኑ ግንባር ቀደም ተላላኪ መሆናቸው ፀሐይ የሞቀው ሃቅ ከሆነ ሰነባብቷል፡፡

ምንም እንኳን ሰውዬው በቀድሞው የግብጽ መንግሥት እየታገዙ የኢትዮጵያ ፀረ-ሰላም ኃይሎችንና ሽብርተኞችን በመመልመል፣ በማደራጀት፣ በማሰልጠንና ወደ ሀገራችን አስርገው በማስገባት እድገታችንን ለማሠናከል ቢወጡና ቢወርዱም፣ ተስፋቸው ግን ጉም ከመዝገን የዘለለ አልሆነም፡፡ ከንቱ መፍጨርጨራቸው በመንግሥታችን በሳል አመራር፣ በሕዝባችን ንቁ ተሳትፎ እንዲሁም በጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችንና በፀጥታ ኃይሎች ቅንጅታዊ ሥራ እንዳያንሰራራ ተደርጎ ድባቅ ተመትቷል፡፡

አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ በአባይ ጉዳይ ላይ በየወቅቱ "የጦርነት ተንታኝ" ሆነው የከረሙበት ሌላኛው ምክንያት ደግሞ የሰውዬው ግብዝ አላዋቂነት ነው፡፡ በእርሳቸው አስገራሚ አስተሳሰብ የዓለም መንግስታት ሁሉ የተሳሳተ መንገድን የሚከተሉ ሲሆን፣ ሰውዬው ግን ብቸኛውና ትክክለኛው መሪ ነኝ ብለው የሚያስቡ ናቸው፡፡… ለነገሩ አበው "ድሃ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ኖሮ፣ ንጣት ይገድለው ነበር" ያሉት ይትብሃል ዝም ብለው የተናገሩት አይደለም–ለእንዲህ አይነቱ የቅዥት ዓለም ሰው ምላሽ እንዲሆን አስበው እንጂ፡፡.. ኧረ ለመሆኑ አንዴ አስመራ ሌላ ጊዜ ደግሞ ምጽዋ ቤተ- መንግሥት ተደብቀው ሁሉንም መንግሥታት የሚያብጠለጥሉት የቀጣናችን ጉደኛ ሰው፣ የማንነታቸው ልኬት የማይታወቅ ይመስላቸዋል እንዴ?…

… እርሳቸው እኮ የሀገራቸውን ህዝብ ነፃነትን፣ እኩልነትንና ፍትሕን እንደ እህል ውኃ እንዲጠማ ያደረጉ እንዲሁም ልማትንና ዕድገትን ብሎም ምርጫን ከጐረቤት ሀገሮች እንዲሰማ

ብቻ የፈረዱበት አምባገነን ናቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ በአንድ ወቅት የራሳቸው ዜጎች የሚመላለሱበት ካይሮ ውስጥ ሰላማዊ ሰልፍ የወጡባቸው አይደሉም እንዴ?... “መሰሪ አልየውም” የተባለ የግብጽ ድረ-ገጽ በወቅቱ ይፋ እንዳደረገው፣ ኤርትራውያኑ አዲስ ህገ-መንግሥት እንዲረቀቅና ነፃ የምክር ቤት ምርጫ እንዲካሄድ በመጠየቅ ካይሮ የሚገኘው የአቶ ኢሳያስ ኤምባሲ ውስጥ የመሸጉ ሹማምንቶቻቸውን አፋጠዋቸዋል፡፡... “ወዲ አፎም” ታዲያ ይህ የጥሩና የተወዳጅ መሪ መገለጫ ነውን?...

... ነገሩ ግን በጣም ያሳዝናል፡፡... አይ አቶ ኢሳያስ! ያኔ “ሞቴን ከሙባረክ ጋር ያድርገው” ብለው ወሬ ለማቀበል ካይሮን እንደ ምፅዋ ቤተ-መንግስታቸው እንዳልተመላለሱባት፣ ዛሬ ነገሩ ሁሉ ተገለባብጦ እርሳቸው ላይ ሰላማዊ ሰልፍ የሚወጣበት ከተማ ትሁን?...መቼም “ሲያልቅ አያምር” እንጂ ሌላ ምን ይባላል? (ውድ አቶ ኢሳያስ! በቅንፍ ውስጥ ሆኖ ቢዘገይም “ነፍስ ይማር” ብያለሁ፡፡) ...ቂ.ቂ.ቂ...

ሰውዬው ሕዝባቸውን ላለፉት 21 ዓመታት ለእርዛት፣ ለድህነትና ለድንቁርና የዳረጉት “ምርጥ መሪ” ስለሆኑ ነውን? ብለን ስንጠይቅም፤ የምናገኘው ምላሽ አቶ ኢሳያስ በሌላቸው አቅም በግብዝነት የሚመፃደቁ ከመሆናቸውም በላይ፤ እውነተኛ ብቃታቸው ተፍቆ ሲታይ ሌላ መሆኑ ነው፡፡ እርሱም በግብረ-ሽበራ ሥራ የአል-ሸባብን ስራ ያለ አንዳች አማካሪ ሊሰሩ የሚችሉ “ምርጥ መሪ” መሆናቸው ብቻ ነው፡፡ እንዲያውም ሰውዬው በአሁኑ ወቅት በመዳከም ላይ ያለውንና የምስራቅ አፍሪካውን የአል-ቃዒዳ ክንፍ አል-ሸባብን ሙሉ ስራ ተክተው የመስራት አቅም አላቸው ማለት ይቻላል። አሳማ ቢን ላደን ሞተ በኋላ አል-ቃዒዳ አመራሩን ለመምረጥ በሚሯሯጥበት ወቅት ምናልባትም እርሳቸውም ውስጥ ለውስጥ ለመወዳደር ሳይፈልጉ የቀሩ አይመስለኝም። ይሁንና “አል-ሸባብን” እየመሩ ስለሆኑ፣ በሥልጣን ላይ ሥልጣን ላለመደረብ ብለው ሳይተውት የቀሩ አይመስለኝም።... ሆ!...ሆ!... ውይ የእኔ ነገር!...ምኑን ያሳሰበኛል ጃል?!- ለካስ ሰውዬው “ምርጫ” የሚባል ነገር አይወዱምና?...

...ያም ሆነ ይህ እስቲ ወደ ተነሳሁበት በአባይ ወንዝ ላይ ስላላቸው አቋም አልባ “አቋም” ልውሰዳችሁ፡፡... ቀደም ባሉት ጊዜያት ከነግብጽ ጋር ቤተኛ ሆነው “በአባይ ጉዳይ የግብጽ ደጋፊ ነን” ሲሉ የነበሩት ኢሳያስ አፈወርቂ፤ ከሙባረክ አገዛዝ በኋላ ምን እንደነካቸው ሳይታወቅ ድንገት ብንን ብለው በራሳቸው መገናኛ ብዙሃን “የኢትዮጵያ ሕዝብ በአባይ ውኃ መጠቀም አለበት” አሉ። ጊዜውም እ.ኤ.አ በ15/07/2011 ዓ.ም ነው።...ታዲያ ይህን አባባላቸውን የዚህ ፅሑፍ አንባቢ “ሁለተኛው ምላስ” ብሎ ይያዝልኝ። ታዲያ በወቅቱ ሰውዬው ሕዝባቸው ምንም መረጃ እንዳያገኝ አድርገው ስለ ሰሜን አፍሪካና መካከለኛ ምሥራቅ ቀውስ መናገር ያለብኝ እኔ ብቻ ነኝ” በማለት

በገዛ ቴሌቪዥናቸው ይህን ማውራታቸውን ስሰማ “ወቸው ጉድ!” ከማለት ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበረኝም፡፡...

መቼም ልክ እንደ እኔ ይህን አባባላቸውን የሰማ ሰው በየዋህነት “ሰውየው ስለ ኢትዮጵያ በጐ ነገር ያስባሉን?” የሚል ጥያቄ አንስቶ ከራሱ ጋር ውዝግብ ውስጥ መግባቱ አይቀርም፡፡ እንዲያውም “ሻዕቢያ በሀገራችን ላይ የሚከተለውን ፖሊሲ ቀየረ እንዴ?” በማለት የሚያሰላስል የዋህ ግለሰብም ሊኖር ይችላል፡፡... እርግጥ የሰውዬውን የማደናገሪያ ንግግር በዚህ መልኩ የሚመለከት ሰው ካለ፣ እውነት እውነት እላችኋለሁ ያ ግለሰብ “ሞኝና ተላላ” ነው፡፡ ምክንያቱም እውነታውና የኢሳያስ ማደናገሪያ ለየቅል በመሆናቸው ነው፡፡ የአስመራው አስተዳደር የሀገራችን ደመኛ ጠላት እንዲሁም ዛሬም ቢሆን ኢትዮጵያን የማተራመስ ፖሊሲውን ያልቀየረ የጥቂቶች ስብስብ ነውና፡፡...

... ይህ ሃቅም አቶ ኢሳያስ የዚያ ዕለት ድንገተኛ ንግግራቸው፤ “... የኢትዮጵያ የውኃ መጠን ብዙ ነው፣ አነስተኛ ነው የሚለው ትርጉም የለውም” በማለት ቀደም ሲል “በውኃው መጠቀም አለበት” ሲሉ የተናገሩትን በቀጥታ በማፍረስ አረጋግጠውልናል፡፡ ይህም የሰውዬውን እውነተኛ ፍላጐት ፍንትው አድርጐ የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ ጽሑፍ አቅራቢ እምነት፤ ”የአስመራው ነውጤ” ንግግር ከወትሮው ያልተለየ፣ የቅርብና የሩቁን ያላገናዘበና ዕይታ የሌለው ግልብ ዲስኩር ነው፡፡ ይህ ንግግር ምንም አይነት ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ መሠረት የሌለው ከመሆኑም በላይ፤ ሰውዬው የሁኔታዎች ግብታዊ ሰለባ የሆኑና ፍራቻ የነገሰባቸው መሆኑን ብቻ የሚያመላክት ነው፡፡

አንድ ጤነኛ አዕምሮ ያለው ሰው በወንዙ የመጠቀም መብትን እየገለፀ ባለበት አንደበቱ፣ ተመልሶ ፍትሐዊ ክፍፍልን የሚወስነውን የውሃ መጠን “ትርጉም የለውም” ሊል አይችልም– አዕምሮው ካልተቃወሰ በስተቀር፡፡ ታዲያ ይህ የአቶ ኢሳያስ የማምታታት ተግባር ሻዕቢያ እውነተኛ ፍላጐቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በጎ ነገር ማሰብ ሳይሆን፣ የተለየ የጥፋት መንገድን እየተከተሉ ለመሆኑ አመላካች ነው፡፡ ስለሆነም የአስመራው ቁንጮ በመግቢያዬ ላይ የጠቀስኩላችሁን ወዳጄን አባባል ተጠቅመው፤ ከዚህ በፊት በይፋ ይገልፁት የነበረውን የጥላቻ መንፈስ፣ በማደናገር አካሄድ ቀይረውት በአዲስ መልክ አጠናክረው መቀጠላቸውን የሚገልፅ ከመሆኑ ውጭ ሌላ የሚያስረዳው ነገር የለም፡፡

ለነገሩ ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ የመጠቀም መብቷን ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች ስለሚፈቅዱላት የማንንም ማረጋገጫ ማግኘት አትሻም፡፡ እንኳንስ ለራሳቸው ተራ የፕሮፖጋንዳ ፍጆታ የሚዘባርቁት ኢሳያስ አፈወርቂ ቀርቶ፣ የትኛውም ወገን ቢሆን “መብቷ ነው” ቢልም፣ ባይልም

የሚያመጣው አንዳችም ነገር የለም፡፡ አባባሉ የአስመራው መንግስት “ፖሊሲውን ቀይሯል” የሚያስብለውም አይደለም- የኤርትራ ባለሥልጣናት በመሪያቸው አስተባባሪነት የኢትዮጵያን መንግሥትና ሕዝብ ሰላም የማይፈልጉ ፀረ-ሰላም ኃይሎችን እያስታጠቁና አስርገው የማስገባት ሙከራዎች ላይ ተጠምደው የሚገኙ በመሆናቸው፡ የፖሊሲ ለውጥ አድርገዋል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡ … የትናንትም ይሁን የዛሬ ፖሊሲያቸው ትርምስና ትርምስ ብቻ ስለሆነ፡፡…

የኤርትራ መንግሥት የአቋም ለውጥ አድርጓል ተብሎ የሚወሰደው፣ እያከናወነ ካለው አፍራሽ የትርምስና የትንኮሳ ተግባር እንዲሁም ከአሸባሪዎች ጋሻ ጃግሬነት ራሱን አላቅቆና “አሉ” የሚላቸውን ችግሮች በውይይትና በድርድር ለመፍታት ዝግጁ ሲሆን ብቻ መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ ከዚህ ውጭ የአስመራው መሪ “ዓይኔን ግንባር ያድርገው” የሚል ቅጥፈት አዲስ የቀበሮ ባህታዊ ሆነው ብቅ ባሉበት ርካሽ ኘሮፖጋንዳ (ለዚያውም እርስ በርሱ በሚጋጭ)፤ ሻዕቢያን እንደ ጥላ ሲከተለው የኖረውን የብጥብጥ አባዜ ሊቀይረው አይችልም፡፡

ይህ ዕውነታ ደግሞ ሰሞኑን ተረጋግጧል። የሻዕቢያውያን ትክክለኛው ማንነታዊ መገለጫ ጊዜውን ጠብቆ ብቅ ብሏል። አይጋ ፎረም የተሰኘው ኢትዮጵያዊ ድረ-ገፅ ከመሰንበቻው ባስነበበን ዘገባ የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር ባለሟሎች ሰሞኑን እንደ ሙባረክ ጊዜ ሁሉ ካይሮን የውሃ መንገድ አድርገውት ሽር ጉድ ሲሉ ሰንብተዋል። ሁሌም ቢሆን የሀገራችን ሁለንተናዊ ዕድገት እንቅልፍ የሚነሳው የአስመራው ቡድን፤ በአቶ ኢሳያስ አማካሪ የማነ ገብረአብና በውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው አቶ ኡስማን ሳለህ አማካኝነት “የኤርትራ መንግስት የግብፅን ታሪካዊ የውሃ ባለቤትነትን ይደግፋል” በማለት ገልጿል።

እንግዲህ ይህ “ሶስተኛው ምላሱ” መሆኑ ነው። በዘመነ-ሙባረክ ወቅት የግራስጌውን የተፋሰሱን ሀገራት አዲስ የስምምነት ማዕቀፍን ለሙባረክ መንፈስ ሲል የተቃወመው፣ በግብፅ አብዮት ወቅት ለጊዜ መግዣና ለይስሙላ ‘ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ የመጠቀም መብት አላት’ ያለው የአስመራው ነውጤ ቡድን፤ ዛሬ ደግሞ የሙባረክ ዘመን ተላላኪነቱ አገርሽቶበት የግብፅ ጋሻ ጃግሬ ሆኗል። ምናልባትም ይህ ስሌቱ የላሸቀውን ኢኮኖሚውን ለማገገም የተጠቀመበት ስልት ይሆናል–እንደለመደው የኢትዮጵያን ህዝብና መንግስት በሁከት ከልማት ተግባራቸው ላስተጓጉልላችሁ በሚል ልመና።

ይሁንና እኔ እስከሚገባኝ ድረስ በሙባረክ ጊዜም ቢሆን የኤርትራ መንግስት በቀቢፀ-ተስፋ ከመወራጨት በስተቀር የህዝባችንን የልማት ጉዞ ያደናቀፈበት ጊዜ የለም። እርግጥ ዋነኛው ምክንያት ባይሆንም ሀገራችንን በመውረር የኢትዮ-ኤርትራን ጦርነት እንዲቀሰቀስ የሙባረክ ገፋፊነትና ሎጀስቲካዊ አይዞህ ባይነት በወቅቱ ያለ አቅሙ የልብ ልብ ሰጥቶት እንደነበር የሚዘነጋ

አይደለም። ሆኖም የኢትዮጵያ ህዝቦች ከብዙ ትዕግስት በኋላ የአስመራው መንግስት በመረጠው የጦረኝነት መንገድ አስተናግደውት በአጭር ጊዜ ውስጥ አከርካሪው ተመትቶ በመጣበት እግሩ ተመልሷል። እናም ለሆስኒ ሙባረክ መንግስት ያተረፈላቸው ነገር ቢኖር ቅሌትን ብቻ ነው። ምክንያቱም ሀገራችን በበሳል አመራሯ እየተመራች ሻዕቢያ በተላላኪነት ስሌት ሊፈፅመው ያሰበውን የረጅም ጊዜ ጦርነትን የቀን ቅዠት እንዲሆን በማድረጓ ነው።

ከዚህ የአቶ ኢሳያስ መራር ኪሳራ በኋላም ቢሆን፣ ሰውዬው ከሙባረክ መንግስት ጋር ሆነው በአዲስ መልክ በቀየሱት የትርምስ ስትራቴጂ አማካኝነት ያከናወኗቸው ተግባራት ጠብ የሚል ነገር አላስገኙላቸውም። ሻዕቢያ በተለያዩ ወቅቶች ከወዳደቁበት ቦታ እየለቃቀመ በመመልመል፣ በማሰልጠንና አደራጅቶ በማስታጠቅ ወደ ሀገራችን አስርጎ ሊያስገባቸው የነበሩት አሸባሪዎችና ፀረ-ሰላም ሃይሎች ምንም የፈየዱለት ነገር የለም። በመላው የሀገራችን ህዝብና የፀጥታ ሃይሎች ትብብር የተላኩትን መልዕክት ሳያደርሱ መንገድ ላይ ሊቀሩ ችለዋል።…

…ውድ አንባቢዎቼ “በሶስተኛው ምላሽ” የመሰልኩት የአቶ ኢሳያስ ሰሞነኛው “የግብፅን ታሪካዊ የውሃ ባለቤትነት እንደግፋለን” አጀንዳ ዋጋ ቢስነትን የሚያመላክተውን ፅሑፌን አልቋጨሁትም። በክፍል ሁለት ፅሑፌ ጉዳዩን ይበልጥ አፍታትተን እንመለከታለን።…